# ሰብአ ትካት

ያባት መቃብር አንጣሎ
በገበናው ተጠልሎ
ዓፅም ያለምልም ብሎ
    ዧ ብሎ መተኛት
    በቀን ማንቀላፋት።
ያያት፤ የቅድመአያትን ሕልም ማመንዠግ
መጠቅጠቅ፤ የነበርን ወግ መሰግሰግ።
የሣባ ዘመን ቁስል ብካይ
ላይሽር በቴዎድሮስ ክብረ - ሰማይ
መስለምለም መፍገምገም መከርተስ መላም
ፀዳል - አልቦ መጋም።
ምን ዓይነት አንደበት?
ሰዋሰው ሲሰወሰው ቃላት ያፈጁበት
ልማማቸውን ያደሩበት።
የዘመናት ትንፋግ - ክረጢት
    - ፋደት!
የእጅ እግር ሠንሠለት
    - መተት!
ምን ዓይነት አንደበት? . . .

ኖርን ያላችሁ ሳትወለዱ
ሥር ምሳችሁ ሥር ሳትሰዱ
ያመተ ዓለም ሰዎች ዕድሜ - በላ
    ተቀጥላ።
በሺ ዘመን እግሮች መውተርተር
በከርሞ ጥጃነት መግተርተር
በልማድ - ልማድ መወጠር

በእምነት - እምነት መታጠብ
በይሉኝታ - ይሉኝታ መታለብ። . . .
የኛችሁ እነሱአችሁ ተሻኩቶ
ድርና ማግ ሁኖ ተስማምቶ
የተቃርኖ ውብ በረከት ሐራም ሁኖ
የመፋጨት አምሓ - እሳት በኖ ተኖ
ዓይን ያላቸው ያስተውሉ ሲጋዙ
መናፍቃን ሰማዕታት ሲወገዙ
ቀለለ፤ - የመጠራጠር ቁምነገር ደርዙ።
ጨለመ፤ - የጥበብ ሻማ ኩራዙ።

በበለው በለው!
በአምታታው በአዋቃው!
በመቶ ዓይነት ጥለፈው
በሺ ዓይነት መትተው
    ልንቃ ሲል
    አንገቱን ሲል።
በቀልቡን ንሣው
በአሣሥቀህ አስለቅሰው
በዓይነ ቁራኛ ጠብቀው
    ቀና ቢል፤ ራሱን ቀጭ
    አቤት ቢልህ፤ ቢማፀንህ
    ጭጭ ... ምጭጭ ... እርጭ።

    ለልማት ሳይሆን ለጥፋት
    ጸሎት ... ምህላ ... ትጋት
    ካንድ ረግቶ ጥንጣን ማድራት። ...
    የገደል ማሚቶ አንቀላፍታ፤
ድምፃችሁን ተንተርሣ
    በእሣት ዳር ምን ይወሳ?
    በሊቃውንት ምን ይነሳ?
መጓዝ ሆነ በዳበሣ ... በደምሣሣ ... በአሰሳ
መልካችሁ አይቀረጽ፤
አይጠፋ ...እየከሣ ... እየሣሣ።
    ተደቡኖ ቀርቶ፤ በእረኛነት ገሣ።

    አይ እናንት፤ ያባቶቻችሁ ልጆች!
        ያያቶቻችሁ ወላጆች
            የዘመን አርማችሁ
        ልዩ ነበር ባንዲራችሁ
    የተነደፈበት የየዋህ ዕድቃችሁ።

................

ደበበ ሰይፉ 1966 ዓ. ም.